

# አቶ ፡ ሰይፉ ፡ ዘለቀ ፡ በዛ ።

1920 ፡ ዓ.ም. ፡ — ፡ 2015 ፡ ዓ.ም. ።

( 1928 A.D. — 2023 A.D. )

በ 1920 ፡ ዓ.ም. ፥ በዘመነ ፡ ዮሐንስ ፥ ሚያዝያ ፡ 2 ፡ ቀን ፥ ማግሰኞ ፡ ዕለት ፡ ሰይፈ ፡ ሚካኤል ፡ ዘለቀ ፡ ተወለዱ ።

እናታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ደብሪቱ ፡ ተሰማ ፡ ዘለሌ ፡ እና ፡ አባታቸው ፡ አቶ ፡ ዘለቀ ፡ በዛ ፡ በሚኖሩበት ፡ ደበ ፡ ጎጆ ፡ በሚባል ፡ ቦታ ፥ የበኵር ፡ ልጃቸው ፡ አቶ ፡ ሰይፉ ፡ ዘለቀ ፥ ደበ ፡ ጎጆ ፡ ይገኝ ፡ ለነበረው ፡ ለሚካኤል ፡ ታቦት ፡ ተሰጥተው ፡ ክርስትና ፡ ተነሡ ።

የመዠመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርታቸውን ፡ ጅማ ፡ እና ፡ ዐምቦ ፡ ተምረው ፡ ኹለተኛ ፡ ደረጃም ፡ በ"አድቬንቲስት ፡ ሚስዮን ፡ ቀበና" ፡ አቃቂ ፡ አጠናቀው ፥ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በሀገር ፡ ውስጥ ፡ "ዩኒቨርስቲ" ፡ ስላልተቋቋመ ፥ ለከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ ኼደው ፡ በሕዝብ ፡ ጤና ፡ ጥበቃ ፡ ኹለተኛ ፡ ("ማስተርዝ") ፡ ዲግሪያቸውን ፡ እንዳገኙ ፥ በመንግሥት ፡ ጥሪ ፥ ላገልግሎት ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ተመለሱ ። ጤና ፡ ጥበቃ ፡ ሚኒስቴር ፡ እንዲያገለግሉ ፡ ሲመደቡ ፥ አቶ ፡ ሰይፉ ፡ ዘለቀ ፣ አቶ ፡ ኀይሉ ፡ ሰብስቤ ፡ እና ፡ አቶ ፡ ዮሐንስ ፡ ጽጌ ፡ በመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ በ"ዩኒቨርስቲ" ፡ ደረጃ ፡ የጤና ፡ ባለሙያዎች ፡ ሦስቱ ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ። ስለዚህም ፡ የጤና ፡ ጥበቃ ፡ ባለሙያዎች ፡ ማሠልጠኛ ፡ ለማቋቋም ፡ ከባልደረቦቻቸው ፡ ጋራ ፡ በመኾን ፡ የኢትዮጵያ ፡ የመዠመሪያ ፡ የጤና ፡ ጥበቃ ፡ ባለሙያዎች ፡ ማሠልጠኛ ፡ ክፍልን ፡ እንዲሁም ፡ ሀገራዊ ፡ የነርስ ፡ ሙያ ፡ ምክር ፡ ቤትንና ፡ ኮሌጅን ፡ በተጨማሪም ፡ የጐንደር ፡ ጤና ፡ ጥበቃ ፡ ኮሌጅንና ፡ ማሠልጠኛ ፡ ማእከልን ፡ ቈርቍረው ፡ መሥርተዋል ። ከዚያም ፥ ከጤና ፡ ጥበቃ ፡ ባለሙያዎች ፡ ማሠልጠኛና ፡ ምደባ ፡ ክፍል ፡ ኀላፊነት ፡ የወባ ፡ ማጥፊያ ፡ ድርጅትን ፡ በበላይነት ፡ እንዲመሩ ፡ ኀላፊነት ፡ ተሰጣቸው ። አቶ ፡ ሰይፉ ፡ ዘለቀ ፥ በሙያቸው ፡ ኢትዮጵያን ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ሌሎች ፡ የአፍሪቃ ፡ አገሮችንም ፡ አገልግለዋል ። በወቅቱ ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ በተመሠረተው ፡ ባዲሱ ፡ የአፍሪቃ ፡ አንድነት ፡ ድርጅት ፡ የጤና ፡ ጥበቃ ፡ ኮሚቴ ፡ አማካሪ ፡ ኾነው ፡ ሠርተዋል ። በመቀጠል ፥ በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ዓለም ፡ ዐቀፍ ፡ የጤና ፡ ድርጅት ፡ ተቀጥረው ፡ በናይጄሪያ ፡ በኡጋንዳ ፡ እና ፡ በኮንጎ ፡ ብራዛቪል ፡ ባማካሪነት ፡ ሠርተዋል ።

በዚህ ፡ ሥራቸው ፡ ላይ ፥ በተባይ ፡ ምክንያት ፡ በጤናም ፡ ኾነ ፡ በግብርና ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ችግር ፡ የታዘቡት ፡ አቶ ፡ ሰይፉ ፡ ዘለቀ ፥ ከተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ጤና ፡ ድርጅት ፡ ተሰናብተው ፡ አገራቸውን ፡ በዚህ ፡ ዘርፍና ፡ በንግድ ፡ በኩል ፡ ለማገልገል ፡ ተመልሰው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገቡ ። በኢትዮጵያ ፡ የመዠመሪያ ፡ የተባይ ፡ ማጥፊያ ፡ ድርጅት ፡ "ኢትዮ ፡ ፔስት ፡ ኮንትሮል"ን ፡ አቋቁመው ፥ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እያሉ ፥ የደርግ ፡ ወታደራዊ ፡ አገዛዝ ፡ ሲመሠረት ፥ አቶ ፡ ሰይፉ ፡ ወደ ፡ ስደት ፡ አመሩ ። በመዠመሪያ ፡ ጅቡቲ ፡ በነበረው ፡ የ"ኢትዮ ፡ ተባይ ፡ ማጥፊያ" ፡ ቅርንጫፍ ፡ ሲሠሩ ፡ ቈዩ ። እዚያም ፡ ሳሉ ፥ ከሌሎች ፡ ጋራ ፡ ኾነው ፡ ርሾ–E.R.S.H.O. ፡ "Ethiopian Relief and Self Help Organization" ፡ የሚባል ፡ ድርጅትን ፡ መሥርተው ፥ በባቡር ፡ በግመል ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ጅቡቲ ፡ የሚገባው ፡ ወጣት ፡ ስደተኛ ፥ ድጋፍን ፣ ሕክምናንና ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የሚኼድበትን ፡ መንገድ ፡ የሚሰጥ ፡ አግልግሎት ፡ አበረከቱ ። ፈረንሳይ ፡ ከጅቡቲ ፡ ስትወጣና ፥ በኢትዮጵያም ፡ በጅቡቲም ፡ አለመረጋጋት ፡ ሲስፋፋ ፥ አቶ ፡ ሰይፉ ፡ እና ፡ ባልተቤታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ አንጄሊና ፡ ማንጎ ፡ ወደ ፡ ብሪታንያ ፡ ተሰደዱ ። ከዚያም ፥ ጡረታ ፡ እስከሚወጡ ፡ ድረስ ፥ በተላያዩ ፡ አፍሪቃ–ዐቀፍ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ድርጅቶች ፡ ባስተዳዳሪነት ፡ በኬንያም ፡ በታንዛንያም ፡ አገልግለዋል ።

አቶ ፡ ሰይፉ ፡ ዘለቀ ፥ በሕይወታቸው ፡ ረዥም ፡ የውጣ ፡ ውረድ ፡ ጕዞ ፥ ከ 60 ፡ ዓመታት ፡ በላይ ፡ ዐብረዋቸው ፡ ከቈዩት ፡ ከባልተቤታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ አንጄሊና ፡ ማንጎ ፡ ጋራ ፡ ኹለት ፡ ልጆችን ፡ አፍርተው ፣ አሳድገው ፣ አስተምረው ፣ የልጅ ፡ ልጅ ፡ አይተው ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ በፍቅር ፡ በደስታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያመሰገኑ ፡ ኖረዋል ። የዘመድ ፡ አዝማድ ፡ አባት ፣ ለሀገር ፡ ሾራት ፡ የታከቱ ፡ ሰይፈ ፡ ሚካኤል ፡ ዘለቀን ፡ ነፍሳቸውን ፡ ይማር ፥ በዐጸደ ፡ ገነት ፡ ያኑርልን ፤ አሜን ❖